የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia

# በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተዘጋጀ የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ  የሲቢኢ ብር ዋና ወኪሎች እና ወኪሎችን የሚያሸልም ዓመታዊ መርሀ ግብር

****************

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ የሲቢኢ ብር ዋና ወኪሎች እና ወኪሎችን የሚያሸልም ዓመታዊ መርሀ ግብር አዘጋጅቷል፡፡

በዚህ መርሀ ግብር ባንኩ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ

- ከእያንዳንዱ ዲስትሪክት አምስት አምስት ወኪሎች፣
- ከአጠቃላይ የባንኩ ዲስትሪክቶች የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ ሶስት ወኪሎች እና
- የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ ሶስት ዋና ወኪሎች ሽልማት ያገኛሉ፡፡

## 1. የሽልማት መስፈርት

### 1.1. ወኪሎች

ቀጥሎ በሚገኘው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሠረት የሲቢኢ ብር ወኪሎች በዋነኛነት በሚሰጧቸው አገልግሎቶች በተቀመጠው መመዘኛ ነጥብ መሠረት በጠቅላላ ከመቶው በሚያገኙት ነጥብ የላቀ ወጤት የሚያስመዘግቡት አምስት ወኪሎች ከእያንዳንዱ የባንኩ ዲስትሪክት ተሸላሚ ይሆናሉ፡፡

| የአገልግሎት አይነት | መለኪያ መስፈርቶች | |
|---|---|---|
| | የሚይዘው ነጥብ (100%) | ዓመታዊ አፈፃፀም |
| ገንዘብ ማስገባት | 25% | በትንሹ 814,000 ዓመታዊ ግብይት ማከናወን |
| ገንዘብ ማውጣት | 10% | በትንሹ 345 ዓመታዊ ግብይት ማከናወን |
| ቢል ክፍያ | 20% | በትንሹ 18,355 ዓመታዊ ግብይት ማከናወን |
| ደንበኛ ማፍራት | 10% | በትንሹ 4,035 አዲስ ደንበኞችን ማፍራት |
| ቋሚ ደንበኛ | 15% | የወኪሉ ደንበኞች ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ አገልግሎት ማግኘት አለባቸው |
| ስልጠና መውሰድ | 10% | ባንኩ የሚያዘጋጃቸውን ሁሉንም ስልጠናዎች መውሰድ |
| በወኪል ሂሳብ የሚገኝ የገንዘብ (E-Money) መጠን | 10% | በአማካኝ በቀን ውስጥ ብር 7,000 (E-Money) በወኪሉ ሂሳብ ሊገኝ ይገባል |

## 1.2. ዋና ወኪሎች

ቀጥሎ በሚገኘው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሠረት የሲቢኢ ብር ዋና ወኪሎች በዋነኛነት በሚሰጧቸው አገልግሎቶች በተቀመጠው መመዘኛ ነጥብ መሠረት በጠቅላላ ከመቶው በሚያገኙት ነጥብ የላቀ ወጤት የሚያስመዘግቡት ሶስት ወኪሎች ተሸላሚ ይሆናሉ፡፡

| የአገልግሎት አይነት | መለኪያ መስፈርቶች | |
|---|---|---|
| | የሚይዘው ነጥብ (100%) | ዓመታዊ አፈፃፀም |
| በዋና ወኪሉ ሥር የሚገኙ ወኪሎች አማካኝ አፈፃፀም | 30% | ለወኪሎች የተቀመጠውን አማካኝ አፈፃፀም 100% ማሳካት |
| ወኪል ምልመላ | 15% | በትንሹ 47 ወኪሎችን መመልመል |
| ቋሚ ወኪል (Active Agent) ምልመላ | 10% | በወር ቢያንስ ሶስት ቋሚ (Active) ወኪሎች ማፍራት |
| የወኪሎችን አስፈላጊ መረጃዎች አሟልቶ መያዝ | 10% | የሁሉንም ወኪሎች አስፈላጊ መረጃዎች አሟልቶ መያዝ |
| በዋና ወኪል ሂሳብ የሚገኝ የገንዘብ (E-Money) መጠን | 20% | ብር 100,000 (E-Money) በዋና ወኪሉ ሂሳብ ሊገኝ ይገባል |
| ስልጠና መውሰድ | 10% | ባንኩ የሚያዘጋጃቸውን ሁሉንም ስልጠናዎች መውሰድ |
| ሪፖርት ማቅረብ | 5% | በሳምንት አንድ ጊዜ (በሩብ ዓመት 12) ሪፖርት ማቅረብ |

# 2. ሽልማት

## 2.1. የወኪሎች ሽልማት

ወኪሎች በተቀመጠላቸው መስፈርት መሠረት ተገምግመው በየዲስትሪክቱ የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡት አምስት ወኪሎች ቀጥሎ የተመለከተውን ሽልማት በደረጃቸው የሚያገኙ ይሆናል፡፡

| ደረጃ | ሽልማት |
|---|---|
| 1 | ላፕቶፕ እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| 2 | አነስተኛ ፕሪንተር እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| 3 | የሞባይል ቀፎ እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| 4 እና 5 | ክሪስታል እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| ከ5ኛ በላይ | የእውቅና ምስክር ወረቀት |

## 2.2. በባንክ ደረጃ ከአጠቃላይ የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ ወኪሎች ሽልማት

| ደረጃ | ሽልማት |
|---|---|
| 1 | ሞተር ሳይክል እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| 2 | አነስተኛ ጄኔሬተር (3KW)፣ የሞባይል ቀፎ እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| 3 | አነስተኛ ጄኔሬተር (3KW) እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |

## 2.3. የዋና ወኪሎች ሽልማት

ባንኩ ባስቀመጠው መስፈርት መሠረት በአፈፃፀማቸው የላቁ ሶስት ዋና ወኪሎች በደረጃቸው የሚከተለውን ይሸለማሉ፡፡

| ደረጃ | ሽልማት |
|---|---|
| 1 | አዲስ የቤት መኪና እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| 2 | ላፕቶፕ እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |
| 3 | ፕሪንተር እና የኮፒ ማሽን እና የእውቅና ምስክር ወረቀት |

በግብይት ማጭበርበር ድርጊት መሳተፍ ከሽልማት እጩነት ያስወጣል፡፡

ደንብና ግዴታዎች ተፈፃሚ ናቸው፡፡